oromiabank.com

# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብና ለመምረጥ የወጣ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ

**ሕዳር 2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

Oromia Bank
Baankii Oromiyaa ኦሮሚያ ባንክ

# ኦሮሚያ ባንክ አ.ማ.

# የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብ እና ለመምረጥ የወጣ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ

## መግቢያ

አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች መሰረት፣ የባንኮችን የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የመምረጥ ስልጣን በባንኮቹ ባለአክሲዮኖች ላይ የተጣለ ኃላፊነት በመሆኑ ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኮርፖሬት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/91/2024 ባንኩ ለዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ዕጩ ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉ ዕጩዎች፣ በጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አማካኝነት የሚመረጡበት ፖሊሲና የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀትና በጠቅላላ ጉባኤ ማፀደቅ የሚኖርበት መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ፤

የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ ሂደት ግልጽነት፣ ፍትሃዊነት እና ተዓማኒነት እንዲኖረው ማድረግ የመልካም አስተዳደርን አበይት መርሆዎች ለማጉላትና ለመተግበር መሳሪያ በመሆን የሚያገለግል መሆኑ በመታመኑ፣

የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በመሆን የሚያገለግሉ ተገቢ እና ብቁ እጩዎችን የሚያቀርብ ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴን ማቋቋም፣ ብቁና ተገቢ የቦርድ አባላትን ለመምረጥ የሚያስችል ስለሆነ ለባንኩ መልካም አስተዳደር መስፈን አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ታማኝነት፣ የአመራር ክህሎት እና ብቃት ያላቸው ዕጩዎችን የማስጠቆምና ማስመረጥ ፤ ተግባርና ሐላፊነት ያለበት መሆኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣው የኮርፖሬት መመሪያ ቁ. ኤስቢቢ/91/2024 በግልፅ የተመለከተ በመሆኑ እና የኮሚቴውን ተግባርና ኃላፊነት መወሰኑ አስፈላጊ በመሆኑ"

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣው የኮርፖሬት አስተዳደር መመሪያ ቁ. ኤስቢቢ /91/2024 ድንጋጌዎች መሠረት፣ ህዳር 27 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው የባንኩ 16ኛ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ቀርቦ ይህ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ ጸድቋል፡፡

## 1. ርእስ

ይህ ሰነድ ''የኦሮሚያ ባንክ አ.ማ. የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብና ለመምረጥ የወጣ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ '' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜዎች

አገባቡ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር፣ በዚህ ሰነድ መሠረት፤

2.1. “**ባንክ''** ማለት ኦሮሚያ ባንክ አ.ማ. ነው፡፡

2.2. **“ቦርድ''** ማለት የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

2.3. **“ዳይሬክተር''** ማለት የባንኩ ዲሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፡፡

2.4. **“ሠራተኛ''** ማለት የባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ፤ የባንኩን የዕለት ተዕለት ተግባራትን ለማከናወን የተቀጠረ ወይም የተሾመ ማናቸውም ሌላ ግለሰብ ማለት ነው፡፡

2.5. **“ጠቅላላ ጉባኤ''** ማለት የባንኩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው፡፡

2.6. **“ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን''** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የባንኩን ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል 2 በመቶ ወይም ከዚህ በላይ በባለቤትነት የያዘ ባለአክሲዮን ማለት ነው፡፡

2.7. **“ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮነን''** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የባንኩን ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ከ2 በመቶ ያነሰ በባለቤትነት የያዘ ባለአክሲዮን ማለት ነው፡፡

2.8. **“አንድ የአገልግሎት ዘመን”** ማለት ከሶስት (3) ዓመታት የማይበልጥ ጊዜ ነው።

2.9. **“ገለልተኛ ዳይሬክተር”** ማለት በባንኩ በማንኛውም አስተዳደር ውስጥ የማይሳተፍ፣ የቦርድ አባል ሆኖ የቦርድ አባልን ነጻ እና ሚዛናዊ አስተያየት ከሚያዛባ ማንኛውም አይነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ የፖለቲካና ሌሎችም ተፅዕኖዎች ነጻ የሆነ፣ ቀጥተኛ ወይም

ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ባለአክሲዮን ያልሆነ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም የባንኩ ሠራተኛ ያልሆነ ወይም ከእነዚህ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌለው፣ ከባንኩ ጋር ማንኛውም አይነት የውል ግዴታ ባለው ድርጅት ውስጥ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ያልሆነ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በፍርድ ቤትም ሆነ ከፍርድ ቤት ውጪ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ማንኛውንም አይነት የህግ ክርክሮች በባንኩ፣ በባንኩ እናት ድርጅት ወይም በባንኩ ተቀጽላዎች ላይ ያላቀረበ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከባንኩ ጋር ማንኛውንም የቢዝነስ፣ የንግድ እና ሙያዊ ግንኙነቶች ያላደረገ፣ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 2.9 መሰረት የተቀመጠውን መስፈርት ሙሉ ለሙሉ የሚያሟላ ማለት ነው ፡፡

2.10. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ህጋዊ ሰው ማለት ነው።

2.11. **"ኮሚቴ''** ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣው የኮርፖሬት መመሪያ ቁ. ኤስቢቢ/91/2024 መሰረት በጠቅላላ ጉባዔ ላይ የሚመረጠው ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

2.12. በተባዕት ፆታ የተነገረው አገላለፅ ለእንስት ፆታም ያገለግላል፡፡

## 3.ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

3.1. የዲሬክተሮች ቦርድ አባልት ምርጫ በሚካሄድበት ጉባኤ ላይ፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጊዜያዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴን ይመርጣል፡፡

3.2. የጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር አምስት ሲሆን፣ ከአምስቱ መካከል ቢያንስ ሁለቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3.3. ኮሚቴው በስራ ላይ ካለው የባንኩ ቦርድ ነፃ መሆን ያለበት ሲሆን፣ በቀጥታ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ ይሆናል፡፡

3.4. ጠቅላላ ጉባኤው ለኮሚቴ አባልነት እስከ አሥር ዕጩዎችን የሚጠቁም ሲሆን፣ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙትን አምስቱን በኮሚቴነት ይሰይማል፡፡

3.5. ጠቅላላ ጉባኤው ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የሚመርጠው በሚስጢራዊ ድምጽ  አሰጣጥ ስርዓት ነው፡፡

## 4. ለጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ የሚያበቁ መመዘኛዎች እና የኮሚቴው አወቃቀር

4.1. የኮሚቴው  አባላት፡-

ሀ) የባንኩ ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው፤

ለ) የባንኩ ሰራተኞች ሊሆኑ አይችሉም፤

ሐ) የኮሚቴው አባል በመሆን የመስራት ፍላጎት ሊኖራቸው  ይገባል፤

መ) እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ረ/ ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አፈፃፀም ተገቢነት ያላቸውን የአሠራር መመሪያዎችን የሚገነዘቡ መሆን አለባቸው፤

ሰ/ ቢቻል ከጉዳዩ ጋር የተገናኘ ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

4.2. በስራ ላይ  ያሉ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የኮሚቴው አባል በመሆን ሊመረጡ አይችሉም፡፡

4.3. የኮሚቴው አባላት ለቦርድ አባልነት በዕጩነት ሊቀርቡ አይችሉም፤

4.4. ኮሚቴው ሊቀመንበር እና ጸሐፊውን ከአባላቱ መካከል  ይመርጣል፡፡

## 5. የዲሬክተሮች ቦርድ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተጣሉበት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ፤

5.1. ብቁ የቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብ እና ለማስመረጥ የሚያስችል ግልፅ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ አለበት፤

5.2. በጠቅላላ ጉባኤው ላይ ፖሊሲውንና የአሠራር መመሪያውን ማጸደቅና ጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የማስመረጥ አጀንዳን በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፤

5.3. ከጉባዔው በፊት መልምሎ ያዘጋጃቸውን እጩ ገለልተኛ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዝርዝር ለአስመራጭ ኮሚቴው ያስረክባል፤

5.4. ለጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

## 6. የጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

ኮሚቴው፡-

6.1. ለቦርድ አባልነት ዕጩዎችን የማስጠቆምና የማስመረጥ ኃላፊነት አለበት፤

6.2. የጥቆማና ምርጫው ሂደት ግልጽ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ በሆነ መልኩ መከናወኑን፣ እንዲሁም ሂደቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን ጨምሮ በሀገሪቱ ሕጎች እና በዚህ ፖሊሲና የአሠራር መመሪያ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል።

## 7. የጊዜያዊ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ጸሀፊ ዋና ተግባራት

7.1. የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ የጥቆማና የምርጫ ሂደቱን በዋናነት ይመራል።

7.2. የኮሚቴው ጸሀፊ፣ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን በተመለከተ በእጩነት የቀረቡትን ዝርዝር፣ ያገኙትን ድምጽ እና የተመረጡትን ከነተጠባባቂዎቻቸው በመለየት የኮሚቴው አባላት የተፈራረሙበትን ሰነድ ለጉባኤው ጸሀፊ ያቀርባል።

## 8. የእጩዎች ጥቆማ እና የምልመላ ሂደት

### 8.1. እጩዎችን በምድብ ማስቀመጥ

የቦርድ ምልመላና አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴ(ኮሚቴው) ከዚህ በታች በተገለጸው መንገድ በሦስት ምድብ እጩዎች፣ ያስጠቁማል፣ ይመለምላል፡፡

8.1.1. ምድብ አንድ ላይ ከቦርዱ አጠቃላይ መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚሆነውን ተጽዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ፤

8.1.2. ምድብ ሁለት ላይ ከቦርዱ አጠቃላይ መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚሆነውን በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚጠቆሙና የሚመረጡ፤

8.1.3. ምድብ ሶስት ከጠቅላላው የቦርድ አባላት መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው በዕጩነት ለኮሚቴው ከተላለፉት መካከል በሁለም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ገለልተኛ የቦርድ አባላት ሊሆኑ ይገባል።

8.1.4. ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች በማይኖሩበት ጊዜ ኮሜቴው ከላይ ከተዘረዘሩት ምድቦች ውስጥ ምድብ ሁለት እና ሶሰት ላይ በተገለጸው ሁኔታ ብቻ እጩዎችን ይመለምላል፡፡

### 8.2. የእጩዎች ብዛት፣

ኮሚቴው በእያንዳንዱ ምድብ ለሚኖሩ ዳይሬክተሮች 2 (ሁለት) ዕጥፍ የሚሆኑ ጥቆማዎችን ተቀብሎ የተጠቆሙትን በእጩነት ይመለምላል፡፡ ከተጠቆሙት ዕጩዎች ቢያንስ አራት ሴቶችን ይመለምላል፡፡

## 9. የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የመመዘኛ መስፈርቶች፤

በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለቦርድ አባልነት የሚጠቆሙ ግለሰቦች ከታች የተቀመጡትን የእውቀት፣ ልምድ እና ብቃት፣ የታማኝነት፣ የፋይናንስ ጤናማነት፣ ከጥቅም ግጭት ነጻ የመሆን፣ የመወሰን ነጻነት እና ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት ጊዜ የመስጠት መመዘኛዎችን ሊያሟሉ ይገባል፡፡

## 9.1. የእውቀት፣ ልምድ እና ብቃት መመዘኛ

9.1.1. ገለልተኛ ያልሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለመሆን የሚጠቆመው ግለሰብ በዕውቀት፣ ልምድ እና ብቃት ደረጃ ቢያንስ የሚከተለውን ሊያሟላ ይገባል፡-

9.1.1.1. ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በቢዝነስ ስተዳደር፣በባንኪንግ፣ በፋይናንስ፣ በስጋት አስተዳደር፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በኦዲቲንግ፣ በህግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት አስተዳደር ወይም ሰስቴይነቢሊቲ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት ደረጃ ያለው እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤስ ቢ.ቢ./89/2024 መሠረት ቢያንስ የሰባት (7) ዓመታት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፤

9.1.1.2. በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በቦርድ አባልነት በማገልገል ላይ ያለ መሆን የለበትም፡፡

9.1.1.3. ለገለልተኛ ዳይሬክተርነት የሚጠቆመው ግለሰብ በዕውቀት፣ ልምድ እና ብቃት ደረጃ ቢያንስ የሚከተለውን ሊያሟላ ይገባል፡-

9.1.1.4. በባንክ ሙያ፣ በሒሳብ አያያዝ፣ በፋይናንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በቴክኖሎጂ እና ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ በአንዱ ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የማስተርስ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ ሙያዊ ብቃት ያለው፤ እና

9.1.1.5. በፋይናንስ ዘርፍ ወይም ከፋይናንስ ዘርፉ ጋር በተገናኘ በማስተማር/በማማከር ወይም በኦዲት ወይም በስጋት አስተዳደር ወይም በማናቸውም ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው መስኮች ቢያንስ (10) ዓመታት የሙያ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 9.2. የባህሪ እና የስነ-ምግባር መመዘኛ

9.2.1. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው የሚጠቆሙ ግለሰቦች ተዓማኒ፣ መልካም ስም ያላቸው እና ታታሪ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ባህሪ እና ስነ ምግባር ለመወሰን

፡-

9.2.1.1. ዳይሬክተሩ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ቦታዎች እምነት በማጉደል

ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ታሪክ የሌለው መሆን አለበት፤

9.2.1.2. ዳይሬክተሩ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችልበት ወይንም የሚቆጣጠረው ድርጅት ስልጣን ባለው ተቆጣጣሪ የመንግስት አካል የጠየቀውን መረጃ ከደበቀ፣ የተሳሳተ የፋይናንስ ወይም ሌሎች መግለጫዎች ካቀረበ ወይም የተቆጣጣሪ የመንግስት ባለስልጣን መስሪያ ቤት የጠየቀውን የእርምት እርምጃዎች ካላከበረ ወይም የሚጠየቀውን መመሪያዎች ወይም መስፈርቶችን ሳያሟላ የቀረበት አጋጣሚ የሌለው፤ እና

9.2.1.3. ማንኛውም ዳይሬክተር ተጽዕኖ ማሳደር የሚችልበት ድርጅት በፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ የዳኝነት ሥልጣን ባለው አካል ወይም በመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ወይም በባለሙያዎች ተቋም እምነት በመጣስ ጉዳዮች ላይ ተመርምሮ፣ ታግዶ ወይም ተቀጥቶ የማያውቅ እና ሌሎች ተዛማጅ የፋይናንስ ወንጀሎች ላይ ተሳትፎ የሌለው መሆን አለበት።

## 9.3. የፋይናንስ ጤናማነት

9.3.1. የቦርድ አባል ሆነው የሚመረጡ ዳይሬክተሮች በገንዘብ ረገድ ጤናማ መሆን አለባቸው፤ የዳይሬክተሮችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ የሚከተሉት መስፈርቶች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡-

9.3.1.1. ዳይሬክተሩ በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ የባለቤት ድርሻ የያዘበት ድርጅት የኪሳራ ክስ ያልተመሰረተበት ወይም ያልከሰረ፤ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ቦታ ወይም የእሱ ወይም የኩባንያው ንብረቶች በሞግዚት አስተዳዳሪ ያልተያዙበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት በኪሳራ ወይም በባንክ ያልታገደበት መሆን አለበት፤

9.3.1.2. ዳይሬክተሩ በዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ

ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት ድርጅት የባንክ ወይም የሌላ ብድር ግዴታውን ወይም የታክስ ክፍያውን ሳይከፍል ያልቀረ መሆን አለበት፤

9.3.1.3. ዳይሬክተሩ ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት ድርጅት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ባለፉት ሁለት (2) ዓመታት ውስጥ ከማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የተበላሸ የብድር ታሪክ የሌለው መሆን አለበት ፤

9.3.1.4. ዳይሬክተሩ አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ በመጻፉ በማንኛውም ባንክ ሂሳቡ ያልተዘጋበት መሆን አለበት።

## 9.4. ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆን እና የመወሰን ነጻነት

9.4.1. ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚጠቆሙ እጩዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከጥቅም ግጭቶች ነፃ በመሆን በገለልተኝነት እና የአመለካከት ነፃነት በተሞላበት መንፈስ መስራት አለባቸው። በዚሁ መሰረትም፡-

9.4.1.1. ከባንኩ ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ መኮንኖች እና/ወይም በባንኩ ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ላይ በተቀመጡ ሌሎች ግለሰቦች፣ ከማንኛውም የባንኩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክስዮኖች ወይም ወይም ከባንኩ አቅራቢ ደንበኞች ወይም ተወዳዳሪዎች ጋር ማንኛውም ቤተሰባዊ ወይም የስራ፣ የሙያ፣ የንግድ ዝምድና የሌላቸው፤

9.4.1.2. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከባንኩ ጋር ማናቸውም በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጪ ክርክሮች ውስጥ ተሳትፎ የሌለው፤

9.4.1.3. ባለፉት ሁለት (2) አመታት ውስጥ ከባንኩ፣ ከእህት ኩባንያ ወይም ከተቀጽላ ማህበር ወይም ከባንኩ ደንበኞች፣ አቅራቢዎች ወይም ተወዳዳሪዎች ወይም ሌሎች ተቀጽላ ድርጅቶች ጋር የንግድ ወይም የሙያ ወይም የግብይት ግንኙነት የሌለው፣ እና

9.4.1.4. ሌሎች በኢትዮጵያ በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ/የሚታሟላ፤

### 9.5. ጊዜ የመስጠት ቁርጠኝነት

ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመረጡ ግለሰቦች በባንኩ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነቶች ለማከናወን በቂ ጊዜ ለመስጠት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

**9.6.** የባንኩ ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆኖ ለመመረጥ ከላይ በአንቀጽ **9(2)-9(5**) የተቀመጡትን ሊያሟሉ ይገባል፡፡

## 10. የዲሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ ሂደት

10.1. ኮሚቴው ከላይ ምድብ ሶስት ተብሎ ከተቀመጠው ውጭ ለእያንዳንዱ ምድብ ከዚህ በታች በተገለጸው መንገድ የእጩዎች ጥቆማ ይቀበላል፡-

10.1.1. በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተገኘ ባለአክሲዮን እጅ በማውጣት በኮሚቴው ዕድሉ ሲሰጠው ራሱን ወይም ሌላ ባለአክሲዮን ወይም የባንኩን ሠራተኛ መጠቆም ይችላል፡፡

10.1.2. ጠቋሚው ባለአክሲዮን የተጠቋሚውን ሥም፣ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ እንዲሁም ባህሪ መግለጽ እና ይህን ሁኔታ ከዚህ መመሪያ ጋር ከተያያዘው የማረጋገጫ ፎርም ላይ በመዘርዘር እውነትመሆኑን እና ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት ለመውሰድ የተስማማ መሆኑን በፊርማ በማረጋጥ መስጠት አለበት፡፡

10.1.3. የሚጠቆመው እጩ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ፣ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው ማንነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ እና ስራ ልምድ አብሮ እንዲገለጽ ኮሚቴው ያደርጋል፡፡ በዕለቱ ይህንን ማረጋገጥ ካልተቻለ ድርጅቱ በቀጣይ እንዲያሟላ ይደረጋል፡፡

10.1.4. ኮሚቴው በጥቆማ ጊዜ በሚከተሉት የሙያ ዘርፎች የትምህርት ዝግጅት እና ተጨባጭ ልምድ ያላቸው በእያንዳንዱ ዘርፍ ሁለት ግለሰቦች እንዲጠቆሙ ጥረት ያደርጋል፡፡ በአንደኛው ዘርፍ ላይ ሁለት ሰዎች ተጠቁመው ከሆነ፣ በሌሎች ዘርፎች ላይ ጥቆማ ለሚሰጡ ባለአክሲዮኖች ቅድሚያ ዕድል ሊሰጥ ይገባል፡፡ የሙያ ዘርፎቹ ዝርዝር፡- ንግድ ስራ አመራር፤ ባንክ እና/ወይም ፋይናንስ፣ አካውንቲንግ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ሕግ፣

ንግድ አስተዳደር፣ ኦዲቲንግ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ኢንቨስትመንት አስተዳደር ናቸው።

10.1.5. የጥቆማ ሂደቱ በምደብ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱት ቁጥሮች ላይ በእያንዳንዱ ምድብ ሁለት ዕጥፍ ቁጥር እስኪገኝ ድረስ መቀጠል አለበት።

## 11. እጩዎችን መመልመል

11.1. ኮሚቴው በአንቀጽ 10 መሰረት ጥቆማ ከተቀበለ በኋላ፣ ተጠቋሚዎቹ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆናቸውን ካረጋገጠ እና ቢመረጡ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸውን እና ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ማረጋገጫ የፈረሙ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ የተጠቆሙትን ዕጩ አድርጎ በየምድቡ ይመለምላል።

11.2. ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የማያሟሉ ሆነው ባገኛቸው ግለሰቦች ምትክ ደግሞ ከላይ አንቀጽ 9 ላይ በተገለጸው መሰረት ጥቆማ ከተቀበለ በኋላ እንደገና በአንቀጽ 10.1. መሰረት ይመለምላል።

## 12. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ ሂደት

በምድብ ሰስት የተቀመጡት ገለልተኛ ዳይሬክተሮች የሚመለመሉበትን ሥርዓት በርዱ ያወጣል። በዚያ ሥርዓት መሰረት የተመለመሉ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ስም፣ የትምህርት ደረጃ፣ ልምድ፣ የገለልተኛነት ማረጋገጫ እና ሌሎች መረጃዎችን በማካተት ለኮሚቴው ያስተላልፋል።

## 13. የዲሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት

13.1 ኮሚቴው የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ከሚመለከታቸው የባንኩ አካላት ጋር በመተባበር የማከናወን ኃላፊነት አለበት፤

13.2 ኮሚቴው ለቀረቡት እጩዎች ቢያንስ ለእያንዳንዳቸው እስከ 2 ደቂቃ ጊዜ በመውሰድ በስብሰባው ወቅት ለጠቅላላ ጉባኤው ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ፤ የቀረበውን

መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸውን እንዲገልፁ እና የቦርድ አባል በመሆን ለመስራት ፍቃደኛ መሆናቸውን እንዲገልጹ እድል ይሰጣቸዋል፤

13.3 የድምጽ መስጫ ካርዱ /ወረቀቱ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ/ የባለአክሲዮኑን ስም፣

ለ/ የተፈረሙ አክሲዮኖች ቁጥር፣

መ/ የባንኩ ስምና አርማ፣

ሠ/ የባንኩ ማህተም፣

ረ/ ባለአክሲዮኑ ሊመርጣቸው የሚፈልጋቸውን እጩዎች ስም የሚጽፍበት ቦታ፣ እና

ሰ/ ለባለአክሲዮን የፊርማ ቦታ፤

13.4 የድምጽ መስጫ ካርዶቹ ለባለአክሲዮኖች አስቀድሞ መሰራጨት አለባቸው፡፡

13.5 ማንኛውም እጩ የቦርድ አባል በመሆን ለመመረጥ ፈቃደኛ ካልሁነ ወይም በሌሎች ተቀባይነት ባላቸው ህጋዊ ምክንያቶች ከዕጩነት ከተሰረዘ፣ በምትኩ ሌላ እጩ እንዲጠቆም ይደረጋል፡፡

13.6 ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች የሚደረግ ምርጫ፣ በሁሉም ባለአክስኖች የሚደረግ ገለልተኛ ያልሆኑ ዳይሬክተሮች ምርጫ፤ እንዲሁም በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚደረግ የገለልተኛ ዲሬክተሮች ምርጫ ለየብቻው እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

13.7 ባንኩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን ከሌለው የቦርድ ምርጫ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይካሄዳል፡፡

13.8 የምርጫው የመጨረሻ ውጤት ለእያንዳንዱ ዕጩ በተፈረሙ አክሲዮኖች ቁጥር በሚሰጥ ድምፅ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 14. የድምፅ አሰጣጥ ስነ- ስርአት

14.1. ኮሚቴው ከባንኩ የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለባለአክሲዮኖች የድምጽ መስጫ ካርዶችን እና ኮሮጆዎችን የሚያዘጋጅ ሲሆን፣ የሚዘጋጁት ካርዶችና ኮሮጆዎች ለጊዜያዊ የቦርድ ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለብቻው፣ ለቦርድ አባላት ምርጫ ደግሞ ሦስት አይነት ማለትም፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ለሚጠቆሙና ለሚመረጡ፣ በሁሉም ባለአክስዮኖች ተጠቁመው በሁሉም ባለአክስዮኖች ለሚመረጡ ገለልተኛ ያልሆኑ

ዳይሬክተሮች እና በዲሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው ለዕጩነት የቀረቡና በሁሉም ባለአክስዮኖች ለሚመረጡ ገለልተኛ (independent Directors) ለየብቻ ይሆናል፡፡

14.2. ባለአክሲዮኖች በድምጽ መስጫ ካርዶች ላይ መምረጥ የሚፈልጉትን እጩዎች ስም በመጻፍ ፈርመው የድምጽ መስጫ ካርዳቸውን ለምርጫው በተዘጋጀው ኮረጆ ውስጥ ይከትታሉ፤

14.3. ባለአክሲዮኑ በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት የሚያደርግ ምርጫ በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፤

14.4. ከጥቆማዎች በኋላ የመጨረሻ ተመራጮችን ለማወቅ የድምጽ ቆጠራው ለአንድ አክሲዮን አንድ ድምጽ በሚለው መረህ በተፈረሙ አክስዮኖች መጠን መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

14.5. የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ፣ ኮሚቴው ድምጾችን ይቆጥራል፤

14.6. በድምጽ ቆጠራው ውጤት መሠረት ሴት እጩዎች ያልተካተቱ ከሆነ፣ ከወንዶቹ መካከል ዝቅተኛ ድምጽ ባገኙት ምትክ ሁለት የተሻለ ድምጽ ያገኙ ሴት ተወዳዳሪዎች በዲሬክተሮች ቦርድ አባልነት እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

14.7. ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጡ ድምጾችን ቁጥር እንዲሁም ዋጋ የሌላቸውን ድምጽ መስጫ ካርዶችን በአግባቡ ይመዘግባል፡፡ ከዚህም ባሻገር የተሰጡ የድምጽ መስጫ ካርዶች ዋጋ ያጡበትን ምክንያት በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ በትክክል መግለጽ ያለበት ሲሆን፣ የኮሚቴው አባላት ዋጋ ባጡት ካርዶች ላይ ይፈርሙባቸዋል፤

14.8. የድምጽ መስጫ ወረቀቱ ቀጥሎ በተመለከቱት በአንደኛው ምክንያት ዋጋ እንዳጣ ተደርጎ ይቆጠራል፡-

ሀ/ የባለአክሲዮን ስም ያልያዘ ከሆነ፣

ለ/ የባለአክሲዮን የተፈረመ አክሲዮን ብዛት ካልተፃፈበት፣

ሐ/ የባንኩ ስም እና ዓርማ ካልታተመበት፣

መ/ የዕጩው ስም ካልተፃፈበት፤

ሠ/ የመራጩ ፊርማ በተገቢው ሁኔታ ካላረፈበት እና፣

ረ/ ስርዝ ድልዝ ካለበት፤

14.9. የድምጽ ቆጠራ በሚያበቃበት ጊዜ፣ ኮሚቴው ድምጽ የመስጠትና የቆጠራው ሂደት እና ውጤቶቹ ህጋዊ ስለመሆናቸው በተመዘገቡት ቃለ ጉባኤዎች ላይ ፊርማውን በማኖር ያረጋግጣል፡፡

14.10. የተቆጠሩ ድምጾች ማህተም አርፎባቸው በተናጠል ይያዛሉ፡፡

14.11. የድምጽ ቆጠራው ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤው በጉባዔው ቀን ይገለጻል፡፡ ውጤቱን በእለቱ መግለጽ ካልተቻለ፣ በባንኩ ዋና መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በቀጣዩ የስራ ቀን በመለጠፍ ይገለፃል፡፡

**15. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ይህንን መመሪያ በመፈጸም ሂደት ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**16. ማሻሻያ**

ይሄ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብ እና ለመምረጥ የወጣ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊሻሻል ይችላል፡፡

17. **የተፈጻሚነት ቀን**

ይሄ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብ እና ለመምረጥ የወጣ ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት እለት አንስቶ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# የማረጋግጫ ቅጽ

(በጠቋሚ የሚሞላ)

የጠቋሚው ሙሉ ስም-------------------------------------------የአክሲዮን መለያ ቁጥር ----------------

የሚጠቁመው ባለአክስዮን ሙሉ ስም -----------------------------------------

**የትምህርት ደረጃ እና ዘርፍ ፡**

**የስራ**

**ልምድ፡**

**ዕድሜ፡**

**ባህሪ እና ሥነ-ምግባር፡**

ከላይ የተሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ አረጋግጣለሁ፣ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት እወስዳለሁ፣ለምሳሌ ባንኩ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሌላ ጉባኤ ማድረግ ቢያስፈልገው የባንኩን ወጪዎችን ለመሸፈን ቃል ገብቻለሁ፡፡

የጠቋሚው ሥም------------------------------ ፊርማ----------------------- ቀን --------------------

ተጠቋሚ የሰጠው ማረጋገጫ

እኔ ...................................................ከላይ የተሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ አረጋግጣለሁ፣ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት እወስዳለሁ፣ለምሳሌ በተሳሳተው መረጃ ምክንያት ባንኩ ሌላ ጉባኤ ማድረግ ቢያስፈልገው የባንኩን ወጪዎች ለመሸፈን ቃል ገብቻለሁ፡፡ እንዲሁም የቦርድ አባል ለመሆን ፈቃደኛ መሆኔን እየገለጽኩ በአሁኑ ጊዜ የጥቅም ግጭት የሚያሥከትል ፣ የመወሰን ነጻነትን የሚገፋ ወይም ሀላፊነቴን እንዳልወጣ የሚያደርግ የጊዜ ጥበት ሁኔታ ውስጥ ያልሆንኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

የተጠቋሚው ሥም----------------------------------- ፊርማ--------------------------- ቀን--------------